# ሥርዓተ ጸሎት

በዓለም ውስጥ ለሚከናወን ለእያንዳንዱ ድርጊት የራሱ የሆነ ሥርዓት አለው ያለ ሥርዓት የሚካሄድ ተግባር ሊኖር አይችልም ከአለም ውጤቱ ሊያምርና የታሰበውን ግብ ሊያስገኝ አይችልም ዓለም ራሱ በተፈጥሮ ሕግና ሥርዓት ስለሚንቀሳቀስ በእርሱ ላይ የሚከናወነው ሥጋዊና መንፈሳዊ ተግባር ሁሉ በሥነ ሥርዓት ይካሄዳል ።

በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የተፈለገው በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለሚካሄደው የጸሎት ሥነ ሥርዓት ነው ። ቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊትና ሐዋርያዊት እንደ መሆንዋ ፤ ሥርዓትዋም ጥንታዊና ሐዋርያዊ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትመራበት ሥርዓተ ጸሎት ክርስቶስ ለሐዋርያት ያስተማረውና ከሐዋርያት ለ318 ሊቃውንት የተላለፈው ነው ። ጸሎት መቼ በየት? እንዴት? ለማንና ለምን? እንደሚጸለይ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ አስተምሮአል፤ማቴ ፤15 ፤26 ፤ 40 ሉቃ 18 ፤ 9 -14

ከሐዋርያት ቀጥለው የተነሱ ሊቃውንት የጸሎትን አፈጻጸም በጻፉበት ክፍ የጸሎት ጊዜያት ሰባት እንዲሆኑ ሥርዓት ሠርተዋል ። እነርሱም ሀ- ነግህ ከጥዋቱ አሥራ ሁለት እስከ አንድ ሰዓት

ለ ሠለስት ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት

ሐ ቀትር ከቀኑ ስድስት ሰዓት

መ በሰዓት ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት

ሠ ሠርክ ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት

ረ ጊዜ ንዋም ሲተኙ ከምሽቱ 2-3 ሰዓት

ሰ መንፈቀ ሊሊት ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት በነዚህ ጊዜያት መድኅን ክርስቶስ ለሰዎች ደኅንነት ሲል የተቀበላቸውን ጸዋትወ መከራ እያስታወሱ መጸለይ እንደሚገባ ጽፈዋል አስተምረዋል በተለይ የነግህና የሠርክ ጸሎት በቤተ ክርስቲያን መፈጸም እንደሚገባቸውየታዘዘ ሲሆን የቀሩት ግን በማንኛውም ቦታ በቤትም ሆነ በመንገድ ሊፈጸም እንደሚቻል ሥርዓት ተሠርቷል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ሥርዓት በመመራት በነግህ ለኪዳን ፤ በሰዓት ለቁርባን ፤ በሠርክ ለጸሎት በርዋ ክፍት ነው ። በቀሩት ጊዜያት የሚጸለየውን ጸሎት ግን ምእመናን ሁሉ እንደ እየችሎታቸው በያሉበት ቦታ እንዲጸልዩ ታዝዞአል።

በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አብዛኛዎቹ በአሥራ አንድ ሰዓት የጸሎት ፕሮግራም አላቸው ። ካህናቱ ለጸሎት ይገኛሉ ለጸሎት ከሚመጡ ምእመናን ጋር ጸሎት ያደርሳሉ ። በጸሎቱም መጨረሻ የወንጌል ትምህርት ይሰጣሉ ። ይህ አይነቱ የጸሎት ሥነ ሥርዓት ክርስቶስ ያስተማረውና ሐዋርያት የተቀበሉት ስለሆነ ሐዋርያዊ ሥርዓት ነው ። በነግህና በሠርክ በቤተ ክርስቲያን በማኅበር እየተሰበሰቡ መጸለይና ትምህርት ወንጌልን መስማት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ቀዋሚ ሥርዓት ሲሆን እያንዳንዱ ምእመን ባያለበት ቦታ እንደ ጊዜውና እንደቦታው አመችነት የክርስቶስን ሕማሙንና ሞቱን ፤ ትንሣኤውንና ዕርገቱን በአጠቃላይ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ከሞት ወደ ሕይወት ከኃሣር ወደ ክብር ለመመለስ የተቀበለውን ጸዋትወ መከራ እያሰቡ መጸለይ እንደሚገባ በፍትሕ መንፈሳዊ በአንቀጽ 14 ተብራርቶ ተወስኖአል ።

የማኅበር ጸሎት በሚጸለይበት ጊዜና ቦታ የግል ጸሎት መያዝ ከጸሎት ሥነ ሥርዓት ውጭ ስለሆነ ክልክል ነው ለምሳሌ በቅዳሴሰዓት የቅዳሴውን ጸሎት መከታተልና ተሰጥዎ መቀበል ሲገባ የግል ጸሎት ለመያዝ መጽሐፍ ዘርግቶ በማነብነብ ሌሎቹን ምእመናን የሚያስቸግሩ ጥቂቶች አይደሉም ። ቅዳሴው ቅሉ ለወንድና ለሴት ለሽማግሎችና ለሕፃናት የሚጸለይ የማኅበር ጸሎት ስለሆነ ሁሉም በነቂሐ ሕሊና በሰቂለ ልቡና ሁኖ ተሰጥዎውን መቀበል እንጂ ሌላ ሥጋዊ ተግባር ማሰብ ወይም የግል ጸሎት መያዝ ክልክል ነው ። ከግል ጸሎት ይልቅ የማኅበር ጸሎት ይጠቅማል ከማኅበር ጸሎት የግል ጸሎት የበለጠ እንደሚጠቅም የሚያምኑ ሰዎች ቢኖሩ ትዕቢተኞች ናቸው ። ትዕቢትም ዐቢይ በደል ስለሆነ ያስቀጣል ።

በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የሚታይ ሌላም የተዘበራረቀ የጸሎት አፈጻጸም አለ፤ይኸውም በቅዳሴው መጨረሻ ላይ በአንድ በኩል ‘‘ አቤቱ ሕዝብን አንድ ርስትህንም ባርክ ’’ በማለት ቄሱ በሚጸልይበትና ሕዝቡን በሚባርክበት ጊዜ በቅኔ ማኅሌት በኩል ዕጣነ ሞገድን ለመጸንጸል የሚደናገረው የከበሮ ድምፅና የወጣቶች መዝሙር ነው ።

ከዚህ ላይ ዕጣነ ሞገድ አይጸንጸል ፤ ወጣቶችም አይዘምሩ ለማለት አይደለም ። ሁሉም ቅደም ተከተሉን ጠብቆ በሥነ ሥርዓት ይፈጸም ለማለት ነው ። ቄሱ የሠርሆተ ሕዝቡን ጸሎት ለማድረስና ለማሰናበት ከመውጣቱ በፊት ዕጣነ ሞገዱ መፈጸም ይኖርበታል ወይም ዕጣነ ሞገዱ እስኪፈጸም ድረስ ቄሱ የሠርሆተ ሕዝቡን ጸሎት ከመጀመር መታገስ ያስፈልግ ይሆናል ። በማኅሌት በኩል ያለው የከበሮና የጸናጽል ድምፅ ሥራውን ሳይፈጽም በወጣቶች በኩል ሌላ መዝሙር ከተጀመረና በየስፍራው ጩኸት ከበዛ ግን የመዝሙሩፍሬ ሐሳብ ወይም ትምህርት ለአድማጮች ግልጥ ሆኖ ሊሰማ ካለመቻሉም በላይ ዕውቅ የሆነ ሐዋርያዊ ሥነ ሥርዓት ያላትን ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት እንደሌላትና በሥነ ሥርዓት እንደማትማራ ሊያስገምት ይችላል ።

በሌላው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አንዱ ክፍል በምዕራብ በኩል ትምህርት እየሰማና መዝሙር እየዘመረ ሳለ ሌላው ክፍል በምሥራቅ በኩል ምህላ ያደርሳል ትምህርቱ ፤ መዝሙሩና ምህላው ቅደም ተከተሉን ጠብቆ በንጹሕ ልቡና በትሑት ሰብእና ሁኖ በማኅበር ቢጸለይ አገርን ከጥፋት ሰውን ከሞት ይታደጋ





www.ethiopianorthodox.org

ል። ግን ጻድቅ ወይም ጸሎተኛ ለመምሰል በቡድን በቡድን እየተከፋፈሉ አንዱ በምሥራቅ ሌላው በደቡብ እየሆኑ መጮኽ ግን ግብዝነት ነው በግብዝነት የሚፈጸም ጸሎትም ዋጋ ቢስ እንደሆነ በወንጌል ተነግሮአል ማቴ 6 ፤ 5 - 14።

ስለዚህ አንደኛ በቅዳሴ ሰዓት የግል ጸሎት መያዝ ተገቢ አለመሆኑን ማስረዳት ፤ ሁለተኛ በጥዋትና በማታ በቤተ ክርስቲያን የሚደረገው ጸሎተ ማኅበርና ትምህርተ ወንጌል ከአለ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ምእመናን ሁሉ የጸሎቱና የትምህርቱ ተካፋዮች እንዲሆኑ ማድረግ ፤ ሦስተኛ በእሁድና በሌሎችም የበዓላት ቀን በየቤተ ክርስቲያኑ በምህላና በትምህርት እያሳበቡ በአራቱ መዓዝነ ቤተ ክርስቲያን በመጮህ የሚያስቸግሩትን መሰል ሰባክያን ሥርዓት ማስያዝና ለምእመናን ጠቃሚ ትምህርተ ወንጌል መስጠትና የቅዳሴን ፤ የመዝሙርንና የጸሎትን ሥነ ሥርዓት ማስተካከል የቤተ ክርስቲያን ተቀዳሚ ተግባር ነው ። ስለሆነም በዚህ ጉዳይ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና ካህናት በጥብቅ ሊያስቡበት ይገባል ።

ራደ አስረስ

www.ethiopianorthodox.org